የሰ/መ/ቁ 231592

መጋቢት 28 ቀን 2015 ዓ/ም

ዳኞች፡- ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

እንደሻው አዳነ

ተሾመ ሽፈራው

መላኩ ካሳዬ

ነጻነት ተገኝ

አመልካቾች፡- ወ/ሮ ሰናይት መርከቡ - ቀረቡ

ተጠሪዎች ፡- አቶ መስፍን አመሸ - አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል።

<u>ፍ ር ድ</u>

በዚህ መዝገብ የተያዘው ጉዳይ የጋብቻ ንብረት ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ጉዳዩ የተጀመረው በአማራ ክልል ባህር ዳር ወረዳ ፍርድ ቤት የአሁን አመልካች በተጠሪ ላይ ባቀረቡት ክስ ነው።

አመልካች በቀን 24/02/2013 ዓ.ም በስር ፍርድ ቤት ባቀረቡት አቤቱታ ከተጠሪ ጋር ሚያዚያ 3/2002 ዓ.ም በባህላዊ መንገድ ጋብቻ መስርተን በትዳር ቆይተናል፤ በቆይታችን ልጅ ባንወልድም ንብረት አፍረተናል፤ ነገር ግን አብረን በጋብቻ ለመቀጠል ከማንችልበት ደረጃ ስለደረስን ጋብቻው እንዲፈርስ። ንብረትን በተመለከተም በቀን 03/08/2002 ዓ.ም ባደረግነው የጋብቻ ውል መሰረት ከጋብቻ በፊት የአመልካች የግል ንብረት የነበረው በባ/ዳር ከተማ ቀበሌ 11 የሚገኝ የመኖሪያ ቤት የአመልካች የግል ተብሎ እንዲወሰን፤ የተጠሪ የግል ንብረት የነበረው በመራዊ ከተማ የሚገኝ መኖሪያ ቤት የተጠሪ የግል ሀብት ነው ተብሎ እንዲወሰን፤ እንዲሁም ከጋብቻ በኃላ አመልካችና ተጠሪ በጋራ ያፈራነው በአመልካች ስም በአዲስ አበባ ከተማ የሚገኝ

የ40/60 ኮንደሚኒም ቤት የጋራ ነው ተብሎ እንዲወሰን በማለት ከሌሎች የቤት ቁሳቁሶች ዝርዝር ጋር አካተው ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

ተጠሪ በሰጡት መልስ በቀን በቀን 03/08/2002 ዓ.ም ጋብቻ ስንፈጽም ከጋብቻ በፊት በየራሳችን ያፈራነው በባ/ዳር ከተማ ቀበሌ 11 የሚገኝ የመኖሪያ ቤት የአመልካች የግል ንብረት እንዲሆን፤ በመራዊ ከተማ የሚገኝ መኖሪያ ቤት የተጠሪ የግል ንብረት እንዲሆን በጋብቻ ውላችን ላይ መጻፉ የማይካድ ሀቅ ነው፡፡ ነገር ግን ከዚህ በኃላ ግራቀኛችን በአዲስ አበባ ከተማ ቤት መግዛት እንዳለብን ተነጋግረን ወስነን ለዚህ ቤት መግዣ እንዲሆን በመራዊ ከተማ የሚገኘው ቤት እንዲሸጥና በአመልካች ስም የሚገኘው የባ/ዳር መኖሪያ ቤት የባልና ሚስት የጋራ ሀብት እንዲሆን ተስማምተን በመራዊ ከተማ የሚገኘውን ቤት ህዳር 07/2006 ዓ.ም በተደረገ የሽያጭ ውል በብር 215000.00 ሸጠናል፡፡ ከዚህ የቤት ሽያጭ ገንዘብ ብር 200000.00 በአዲስ አበባ 40/60 ኮንደሚኔም መግዣ እንዲሆን በሚል በአመልካች ስም በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በተከፈተው አካውንት ገቢ የተደረገ ሲሆን በተለያዩ ቀናትም ተጠሪ በተጨማሪ ብር 74556.00 ወደዚህ አካውንት ገቢ አድርጌያለሁ፡፡ የኮንደሚኔም መኖሪያ ቤቱም ደርሶን ከአዲስ አበባ ቤቶች ልማት ፕሮጀክት ገዝተናል፡፡ ከዚህ በኃላ አመልካችና ተጠሪ ቀደም ሲል በተስማማነው መሰረት በአመልካች ስም በባ/ዳር ከተማ የሚገኘው መኖሪያ ቤት እና የአዲስ አበባው 40/60 ኮንደሚኔም የጋራ ሀብት እንዲሆን በቤተሰቦቻችን አማካኝነት ውል ፈጽመን በፍርድ ቤት ለማጸደቅ በሂደት ላይ እያለን አመልካች ክስ አቅርባለች፡፡ በመሆኑም የአመልካችም ሆነ የተጠሪ የግል ንብረት የሆነው መኖሪያ ቤት ከጋብቻ በኃላ በጋራ ስምምነት የተቀላቀለ ስለሆነ አመልካች የጋብቻ ውሉን በመጥቀስ የግል ንብረት እንዲሆን ይወሰንልኝ በማለት የጠየቀችው ውድቅ ተደርጎ ንብረቱ የጋራ ነው ተብሎ ይወሰንልኝ፡፡ ይህ የሚታለፍ ከሆነ የ40/60 ኮንደሚኔም የተገዛው የግል ቤቴ ተሸጦ በመሆኑና የአመልካች አንዳችም ኢኮነሚያዊ አስተዋጽኦ የሌለበት በመሆኑ የተጠሪ የግል ንብረት ነው ተብሎ ይወሰንልኝ፡፡ ይህ ታልፎ በኮንደሚኔም ቤቱ የአመልካች አስተዋጽኦ አለበት የሚባል ከሆነም የአመልካች አስተዋጽኦ ከ5% በላይ ባለመሆኑ የኮንደሚኔም ቤቱ በሀራጅ ተሸጦ 95% የተጠሪ ድርሻ ነው ተብሎ እንዲወሰንልኝ፡፡ ፍርድ ቤቱ ይህንንም የማይቀበለው ከሆነ በመራዊ ከተማ ይገኝ

የነበረው ቤት በአሁኑ ሰዓት ከብር 1000000.00 (አንድ ሚሊዮን) በላይ ሊገመት የሚችል በመሆኑ ይኸው ገንዘብ ከአመልካች ድርሻ ላይ ተነስቶ ይከፈለኝ። ይህም ከታለፈ ለኮንደሚኔም ቤቱ ግዥ በአመልካች አካውንት ገቢ ያደረኩት በጠቅላላ ብር 314679.64 የግል ገንዘብ ነው ተብሎ የሀብት ክፍፍል ከመደረጉ በፊት ተጠሪ በቅድሚያ ገንዘቤን መልሼ እንድወስድ ይወሰንልኝ በማለት ተከራክረዋል።

ጉዳዩ በዚህ መልኩ የቀረበለት የስር ፍርድ ቤት ጋብቻው በፍቺ ቀሪ እንዲሆን ከወሰነ በኃላ ንብረትን በሚመለከት ክርክሩንና የግራቀኙን ማስረጃ በመስማት ውሳኔ ሰጥቷል። በሰጠው ውሳኔ በባ/ዳር ከተማ ቀበሌ 11 የሚገኘው መኖሪያ ቤት በጋብቻ ውላቸው የአመልካች የግል ንብረት እንዲሆን ተስማምተው ያስመዘገቡ መሆኑን ግራቀኙ ያልተካካዱ በመሆኑና ተጠሪ በመልሳቸው ከጋብቻ በኃላ ቤቱን በጋራ ለማድረግ በሽማግሌዎች ተስማምተው እንደነበር ነገር ግን በሚመለከተው አካል ያልፀደቀ መሆኑን የገለጹ በመሆኑ ቤቱ የአመልካች የግል ንብረት ነው። በጋብቻ ጊዜ ለቤቱ ዕድሳት የወጣውን የተጠሪ ድርሻ ብር 26675.96 አመልካች ይክፈሉ። በአዲስ አበባ የሚገኘው የ40/60 ኮንደሚኔም በአመልካች ስም የተመዘገበና የተገዛ ቢሆንም በጋብቻ ጊዜ የተፈራ በመሆኑ የጋራ ሀብት ነው፤ ነገር ግን የተጠሪ የግል ቤት ተሸጦ ቀጥታ የግል ገንዘቡ ብር 274,556.00 በአመልካች ስም ለተከፈተ የኮንደሚኔም አካውንት ገቢ የተደረገ በመሆኑ የጋራ ሀብት ክፍፍሉን ከማድረጋቸው በፊት ቅድሚያ አመልካች ይህን ገንዘብ ለተጠሪ ሊመልሱ ይገባል በማለት ወስኗል።

በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት አመልካች ይግባኝ ለባህርዳርና አካባቢዋ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበዋል። ፍርድ ቤቱ ግራቀኙን አከራክሮ በሰጠው ውሳኔ ተጠሪ በመራዊ ከተማ የሚገኘውን የግል ብሎ ያስመዘገበውን ቤት በብር 215000.00 ሽጦ ብር 200000.00 ለኮንደሚኔም ክፍያ የዋለ መሆኑ በስር ፍርድ ቤት የተረጋገጠ ጉዳይ ሲሆን በአማራ ክልል የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 79/1995 አንቀጽ 69(1)(2) አኳያ ሲታይ ባልና ሚስት ከተጋቡ በኃላ አንደኛው የግል ሀብቱ በሆነ ንብረት በለውጥ ያገኘው በግል ገንዘቡ የገዛው ወይም የግል ንብረቱን ሽጦ የሚያገኘው የግል ሀብቱ

እንደሚሆን የሚደነግግ ሲሆን ይህም ሊሆን የሚችለው በግብይት የሚገኘው ንብረት የግል ይባልልኝ ብሎ ጥያቄ ሲያቀርብና ፍርድ ቤት ተቀብሎ ሲያፀድቀው ብቻ ስለመሆኑ በግልጽ ተደንግጓል፡፡ ስለሆነም በመራዊ ከተማ የነበረው ቤት ተሸጦ ለኮንደሚኔም ክፍያ ያዋለ መሆኑ የተረጋገጠ ቢሆንም ከፍሲል በተጠቀሰው የህጉ ድንጋጌ መሰረት ተጠሪ የግል እንዲባልለት ያላቀረበና በግሉ ያልተመዘገበ በመሆኑ የግሉ ሊሆን የሚችልበት አግባብ ሳይኖር የስር ፍርድ ቤት አመልካች የቤቱን ሽያጭ ገንዘብ ብር 274556.00 እንድትመልስ መወሰኑ የህግ ስህተት ነው በማለት ውሳኔውን አሻሽሏል፡፡

በዚህ ውሳኔ ላይ ተጠሪ ይግባኝ ለአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ይግባኙ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 337 መሰረት ተሰርዟል፡፡ ቀጥለው ለክልሉ ሰበር ችሎት ቅሬታቸውን አቅርበዋል፡፡

የክልሉ ሰበር ችሎት ተጠሪ የግል ቤቱ ተሸጦ የተገኘው ገንዘብ ከጋራ ሀብታቸው (ኮንደሚኔም) ጋር የተቀላቀለ ከሆነ ይህን ገንዘብ የማንሳት መብት ሊኖረው ይገባል? ወይስ አይገባም? የሚል ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን አስቀርቦ የግራቀኙን ክርክር መርምሮ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ በሰጠው ውሳኔ የተጠሪ የግል ቤት ተሸጦ የተገኘ ገንዘብ ከጋራ ሀብታቸው ጋር የተቀላቀለ በመሆኑ ይህን የተቀላቀለ ገንዘብ ተጠሪ የጋራ ሀብታቸው ከመከፈሉ በፊት በክልሉ የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 97(2) መሰረት ከጋራ ንብረታቸው ላይ በቅድሚያ የማንሳት መብት አለው፡፡ የገንዘቡን መጠን በተመለከተ ግን የተጠሪ የግል ቤት ተሸጦ የጋራ ለሆነው ኮንደሚኔም ቤት ክፍያ የዋለው ገንዘብ ብር 200000.00 ብቻ መሆኑ የተረጋገጠ ሲሆን ሌላው ብር 74556.00 ለአሁን አመልካች የተላከው ግራቀኙ በትዳር ላይ እያሉ በመሆኑና ይህ ገንዘብ የተጠሪ የግል ሀብት መሆኑን የሚያመለክት ክርክርና ማስረጃ በስር ፍርድ ቤት ስላልቀረበ ተጠሪ ከጋራ ሀብታቸው ላይ የማንሳት መብት የሚኖረው የግል ሀብቱ መሆኑ የተረጋገጠውን ብር 200000.00 (ሁለት መቶ ሺህ) ብቻ ሊሆን ይገባል በማለት የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያሳለፉትን ውሳኔ ሽሮ የወረዳ ፍርድ ቤት ውሳኔን በማሻሻል ወስኗል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ነው። አመልካች ሀምሌ 22 ቀን 2014 ዓ.ም በውሳኔው ተፈፀመ የሚሉትን የህግ ስህተት ዘርዝረው አቅርበዋል። ቅሬታው ተመርምሮ ተጠሪ ገንዘቡ የግል መሆኑን ባላስመዘገበበት ሁኔታ የክልሉ ሰበር ችሎት የግሉን ብር 200000.00 ለኮንደሚኔም ስለከፈለ ይህን ገንዘብ ከጋራ ንብረታቸው ላይ በቅድሚያ የማንሳት መብት አለው በማለት የሰጠው ውሳኔ ከክልሉ የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 69(2) ድንጋጌ አንፃር ተገቢነቱን ለማጣራት በሚል ጉዳዩ ለዚህ ሰበር ችሎት እንዲቀርብና ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት ተደርጓል። በዚህ መሰረት ግራቀኙ የስር ክርክራቸውን በማጠናከር መልስና የመልስ መልስ ተለዋውጠዋል።

ከፍ ሲል በአጭሩ የገለጽነው የጉዳዩን አመጣጥ ነው። በበኩላችን ለሰበር ችሎቱ የተያዘውን ጭብጥ መሰረት በማድረግ የግራ ቀኙን ክርክር ቅሬታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከተገቢው የህጉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምረናል።

እንደመረመርነው ተጠሪ የሚያቀርቡት ክርክር የግሌ የነበረው ቤት ተሸጦ አዲስ አበባ ለሚገኘው የኮንደሚኔም ቤት የዋለ መሆኑ በስር ፍርድ ቤቶች የተረጋገጠና አመልካችም ባቀረበችው ክስ የተረጋገጠ ነው፤ በጉዳዩም ተፈፃሚነት ያለው የክልሉ የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 97(2) እንጂ አንቀጽ 69 አይደለም ስለሆነም ውሳኔው በአግባቡ ነው በሚል ነው። አመልካች በበኩላቸው ተጠሪ የግል ቤቴን ሸጬለሁ በማለት መከራከሪያ የሚያቀርበው ቤቱ በጋብቻ ውስጥ ከተሸጠ ከ 7 ዓመት በታላ ነው፤ ይህ መራዊ የሚገኝ ቤት እንዲሸጥ ከእኔ ጋር የተደረገ ስምምነት የለም፤ ገንዘቡን በተመለከተም ብር 200000.00 ለጋራ ጥቅም ለኮንደሚኔም ቤት ክፍያ የዋለ ነው፤ በቤተሰብ ህጉ አንቀጽ 69(2) መሰረት እንዲመዘገብለት ጥያቄ አቅርቦ አላስመዘገበም ስለሆነም ተጠሪ የጋራ ሀብት ከመከፈሉ በፊት ከጋራ ንብረት ይህን ገንዘብ በቅድሚያ የማንሳት መብት አለው መባሉ ህጉን የተከተለ አይደለም በማለት መከራከራቸውን መዝገቡ ያሳያል።

በመሰረቱ በተሻሻለው የፌዴራሉ ቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 እንዲሁም በአማራ ክልል የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 79/1995 ድንጋጌዎች ይዘት መገንዘብ እንደሚቻለው ባልና ሚስት የንብረት ግንኙነታቸውን አስመልክተው የጋብቻ ውል ሊያደርጉ ይችላሉ። ከተጋቡ በኃላ አንዱ የግል

ሀብቱ በሆነ ንብረት ለውጥ የሚያገኘው ወይም በግል ገንዘቡ የገዛቸው ወይም የግል ንብረቱን ሸጦ የሚያገኘው ገንዘብ የግል ሀብቱ የሚሆን ሱሆን ይህ ግን የሚሆነው የግል ይባልልኝ ብሎ አንደኛው ወገን ጥያቄ አቅርቦ ፍርድ ቤት ሲያፀድቀው ነው። በዚህ መልኩ በጋብቻ ውሉ በተለየ መልኩ ስምምነት እስካልተደረገ ድረስ እንዲሁም የተለወጠው ንብረት ጥያቄ ቀርቦበት እስካልፀደቀ ድረስ የቤተሰብ ህጉ ድንጋጌዎች የተጋቢዎችን የንብረት ግንኙነት የሚገዙ ይሆናል። በፍቺ ጊዜ የንብረት ክፍፍሉም የሚደረገው ይህንኑ ተከትሎ ይሆናል።

በተለይ ትዳር ሲመሰረት የዕድሜ ልክ ጥምረት ይሆናል በሚል ሃሳብ በመሆኑ ተጋቢዎች ለረዥም ዘመን በዚሁ ህጋዊ ጥምረት ስር ይኖራሉ። በዚህ ሂደት ደግሞ የግል የነበረ ንብረት አይነቱ የሚለወጥበት፤ ተሸጦ ሌላ የሚገዛበት፤ ከጋራ ንብረት ጋር የሚቀላቀልበት ዕድል ሰፊ ነው። እንዲህ በሚሆንበት ጊዜ በአይነት የተለወጠው ወይም ተሸጦ የተገዛው አመጣጡን ተከትሎ የግል የሚሆን ቢሆንም ከፍሲል እንደተገለፀው በጋብቻ ውስጥ ከሚፈራ ንብረት ጋር የመቀላቀል እድሉ ሰፊ በመሆኑ የግል እንዲባልለት የሚፈልገው ወገን የግድ ጥያቄውን ለፍርድ ቤት ሊያቀርብና ፍርድ ቤት ሊያፀድቀው ይገባል። ይህ ካልሆነ ግን የታለኛው ንብረት የጋራ ይሆናል፤ ክፍፍልም የሚደረገው የህጉን የዕኩልነት መርህ ተከትሎ ነው።

በአማራ ክልል የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 79/1995 አንቀጽ 69(1) እና (2) ስር በግልጽ እንደተደነገገውም ይህንኑ መሰረት ያደረገ ነው። አንደኛው ተጋቢ የግል ሀብቱ የሆነው ንብረት ተለውጦ የተገኘ ንብረት የግል ሊሆን የሚችለው አዲስ የተገኘው ንብረት የግል ይባልልኝ በሚል ጥያቄ ለፍ/ቤት ቀርቦ የፀደቀ እንደሆነ ብቻ ነው። በዚህ መልኩ በህጉ አግባብ የግል የተባለ ንብረት ከጋራ ሀብታቸው ጋር በተቀላቀለ ጊዜ በአዋጁ አንቀጽ 97(2) መሰረት ከግል ንብረቱ ጋር ተመጣጣኝ የሆነ ገንዘብ ወይም ንብረት ከጋራ ሀብታቸው በቅድሚያ እንዲያነሳ በማድረግ ክፍፍል ይደረጋል። ስለሆነም በክልሉ የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 97(2) መሰረት ተፈፃሚ ሊሆን የሚችለው በቤተሰብ ህጉ አንቀጽ 69(2) እና 84 መሰረት አስቀድሞ በፍርድ ቤት (በፍትህ አካል) ተቀባይነት አግኝቶ የፀደቀ ሲሆን ነው።

በተያዘው ጉዳይ የተጠሪ የግል ንብረት የነበረው የመራዊ ቤት ተሸጦ በግራቀኙ የጋብቻ ዘመን አዲስ አበባ ለሚገኘው የጋራ የ40/60 የኮንደሚኔም ቤት መግዣ ይሆን ዘንድ ብር 200000.00 ገቢ መደረጉ በስር ፍርድ ቤቶች ተረጋግጧል። በዚህ መልኩ የተጠሪ የግል ንብረት ሲለወጥ የግል ይባልልኝ በሚል ተጠሪ በህጉ አግባብ ጥያቄ አቅርበው የፀደቀ ስለመሆኑ የቀረበ ክርክርም ሆነ ማስረጃ የለም። የኮንደሚኔም ቤቱ የጋራ በመሆኑም ግራቀኙ እንዲካፈሉት ተወስኗል። ስለሆነም የኮንደሚኔም ቤቱ በጋብቻ የተፈራ የጋራ ሀብት ነው ተብሎ እኩል እንዲካፈሉት እየተወሰነ የጋራ ለሆነው ኮንደሚኔም ቤት ተጠሪ ከፍለውት ነበር በሚል በህጉ አግባብ የግል እንዲባል ጥያቄ ቀርቦበት ተቀባይነት የገኘ መሆኑ ያልተረጋገጠን ገንዘብ መልሰው እንዲወስዱ የተሰጠው ውሳኔ ከፍሲል የተጠቀሱትን የቤተሰብ ህጉን ድንጋጌዎች አላማና ይዘት የተከተለ አይደለም።

በአጠቃላይ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶች በመራዊ ከተማ የነበረው ቤት ተሸጦ ከሽያጩ ገንዘብ የተወሰነው ለኮንደሚኔም ክፍያ ያዋለ መሆኑ የተረጋገጠ ቢሆንም ተጠሪ የግል እንዲባልለት ያላቀረበና በግሉ ያልተመዘገበ በመሆኑ የግሉ ሊሆን የሚችልበት አግባብ የለም፤ ስለሆነም አመልካች የቤቱን ሽያጭ ገንዘብ እንድትመልስ የሚወሰንበት የህግ አግባብ የለም በማለት የደረሱበት መደምደሚያ እና ያሳለፉት ውሳኔ የሚነቀፍበት የህግ ምክንያት የለም ብለናል። በአንፃሩ የክልሉ ሰበር ችሎት የተጠሪ የግል ቤት ተሸጦ የተገኘ ገንዘብ ከጋራ ሀብታቸው ጋር የተቀላቀለ በመሆኑ ይህን የተቀላቀለ ገንዘብ ተጠሪ የጋራ ሀብታቸው ከመከፈሉ በፊት ከጋራ ንብረታቸው ላይ በቅድሚያ የማንሳት መብት አለው በማለት ያሳለፈው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል ብለናል። ተከታዩንም በአብላጫ ድምጽ ወስነናል።

ው ሣ ኔ

1. የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ 03 -111460 ሰኔ 15/2014 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ተሸሯል።

2. የባህር ዳር እና አካባቢዋ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 03-28001 ህዳር 29/2014 ዓ.ም ያሳለፈው ውሳኔ፤ እንዲሁም የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፍ/ቤት በመ/ቁ 57531 በቀን 25/04/2014 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡

3. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/0

የልዩነት ሃሳብ

ስሜ በሦስተኛ ተራ ቁጥር ላይ የተሰየምኩት ዳኛ ቀጥሎ በተመለከቱት ሁለት ዋና ዋና ምክንያቶች መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ በሚል የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠዉን ዉሳኔ በመሻር በአብላጫዉ ድምጽ በተሰጠ ዉሳኔ አልተስማማሁም፡፡

የመጀመሪያዉ ምክንያት በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 መሠረት የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሚሰጣቸዉ ዉሳኔዎች ላይ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሚኖረዉን ስልጣን የሚመለከት ነዉ፡፡ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 መሠረታዊ የህግ ስህተት ማለት ምን ማለት እንደሆነ ትርጓሜ ይሰጣል፡፡ በአዋጁ በትርጉም ክፍል አንቀጽ 2(4) ላይ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች መገንዘብ እንደሚቻለዉ አንድ ዉሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ለማለት የሚቻለዉ የህገ መንግስቱን ድንጋጌዎች የሚቃረን፣ ህግ ያላግባብ የሚተረጉም ወይም ለጉዳዩ አግባብነት የሌለዉን ህግ የሚጠቅስ፣ ለክርክሩ አግባብነት ያለዉ ጭብጥ ሳይያዝ ወይም ከክርክሩ ጋር የማይዛመድ አግባብነት የሌለዉ ጭብጥ ተይዞ የተወሰነ፣ በዳኝነት ታይቶ ሊወሰን የሚገባዉን ጉዳይ ዉድቅ በማድረግ የተወሰነ፣ በፍርድ አፈፃፀም ሂደት ከዋናዉ ፍርድ ጋር የማይገናኝ ትዕዛዝ የተሰጠበት፣ ጉዳዩን አይቶ የመወሰን የዳኝነት ስልጣን ሳይኖር የተወሰነ፣ የአስተዳደር አካል ወይም ተቋም ከህግ ዉጭ የሰጠዉ ዉሳኔ፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትን አስገዳጅ ዉሳኔ በመቃረን የተወሰነ ሲሆን ነዉ፡፡ በመሆኑም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ በሚል የሰበር አቤቱታ ሲቀርብለት ለአቤቱታዉ ምክንያት የሆነዉ ጉዳይ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ለማለት የሚቻለዉ ዉሳኔዉ/ትዕዛዙ/ብይኑ ከላይ በዝርዝር ከተመለከቱት ሁኔታዎች ዉስጥ ቢያንስ አንዱን ያሟላ ሆኖ ሲገኝ ስለመሆኑ በአዋጁ አንቀጽ 10 ላይ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች የምንገነዘበዉ ነዉ፡፡ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ለሰበር አቤቱታዉ ምክንያት የሆነዉ በክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠ

ዉሳኔ/ትዕዛዝ/ብይን ሲሆን የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታዉን ተቀብሎ በሰበር የማየት ስልጣን የሚኖረዉ ዉሳኔዉ/ትዕዛዙ/ብይኑ የህገ መንግስቱን ድንጋጌዎች፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትን አስገዳጅ ዉሳኔ የሚቃረን ሲሆን እንዲሁም አግባብነት የሌለዉን ህግ በመጥቀስ ወይም ህግን ያላግባብ በመተርጎም የተሰጠ ዉሳኔ/ትዕዛዝ/ብይን ሆኖ ጉዳዩም አገራዊ ፋይዳን የሚመለከት ሲሆን ብቻ ስለመሆኑ የአዋጁ አንቀጽ 10 (1/ሐ/ እና /መ) ድንጋጌዎች ያስገነዝባሉ፡፡ ከዚህም የምንረዳዉ የሰበር አቤቱታ የቀረበበት የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ዉሳኔ ከእነዚህ ሦስቱ ሁኔታዎች ዉጪ ባሉት ሁኔታዎች፣ መሠረታዊ የህግ ስህተትን መስፈርት አስመልክቶ በአዋጁ አንቀጽ 2(4) ላይ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች ዉስጥ አንዱን የሚያሟላ ሆኖ ቢገኝ እንኳን፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን በሰበር የማረም ስልጣን የሌለዉ መሆኑን ነዉ፡፡ ስለሆነም ይህ የፌዴራል ጠቅላይ ሰበር ሰሚ ችሎት የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትን ዉሳኔ/ትዕዛዝ/ብይን መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን ያለመሆኑን በመወሰን ረገድ እነዚህኑ ልዩ ሁኔታዎች ማለትም በአዋጁ አንቀጽ 10(1/ሐ) ላይ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ከግምት ዉስጥ የማስገባት ኃላፊነት ይኖርበታል፡፡ በተያዘዉ ጉዳይ የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ የህገ መንግስቱን ድንጋጌ እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠዉ አስገዳጅ ትርጉም የሚጥስ እንዲሁም አገራዊ ፋይዳ ባለዉ ጉዳይ ላይ የተሰጠ ባለመሆኑ በዚህ ችሎት ሊታረም የሚችል መሠረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሞበታል ለማለት አይቻልም፡፡

ሁለተኛዉ ምክንያት፣ ከላይ የጠቀስኩት እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ይህ ችሎት ዉሳኔዉን የማረም ስልጣን አለዉ እንኳ ቢባል፣ የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በክልሉ የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 97(2) ላይ የተመለከተዉን ድንጋጌ በዋቢነት በመጥቀስ በሰጠዉ ዉሳኔ የተፈጸመ መሠረታዊ የህግ ስህተት መኖር አለመኖሩን የሚመለከት ነዉ፡፡ ተጠሪ በመራዊ ከተማ የነበረዉን የግል ቤቱን ሸጦ ብር 200,000.00 በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በአመልካች ስም በተከፈተዉ ሂሳብ ላይ ገቢ ማድረጉንና ገንዘቡም የአመልካች እና የተጠሪ የጋራ ሀብት ነዉ ተብሎ በተወሰነዉ እና በአዲስ አበባ ከተማ በሚገኝ 40/60 ቤት ግዥ የዋለ ስለመሆኑ አላከራከረም፡፡ ይህም የሚያሳየዉ የግራ ቀኝ የጋራ በሆነዉ ኮንዶሚኒየም ዉስጥ የተጠሪ የግል ገንዘብ የተቀላቀለበት መሆኑን ነዉ፡፡

አብላጫዉ ድምጽ ለዉሳኔዉ መሠረት ያደረገዉ የክልሉ የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 69(1) እና (2) ላይ የግል ሀብት የሆነ ንብረት ባልና ሚስት አብረዉ በሚኖሩበት ወቅት የተለወጠ እንደሆነ እና አንደኛዉ ተጋቢ ንብረቱ የግሌ ነዉ የሚል መከራከሪያ ያነሳ እንደሆነ ብቻ ስለመሆኑ ድንጋጌዉ በግልጽ ያሳያል፡፡ አንደኛዉ ተጋቢ ንብረቱ የተገኘዉ የግል ንብረቱን በመሸጥ በተገኘ ገንዘብ ወይም ግብይት መሆኑን ጠቅሶ ንብረቱ የግሌ ነዉ ተብሎ ይወሰንልኝ የሚል መከራከሪያ ያቀረበ እንደሆነ ክርክሩ ተቀባይነት አግኝቶ ንብረቱ የግሉ ሆኖ ሊወሰን የሚችለዉ ንብረቱ የተገኘዉ ንብረቱ የግሉ መሆኑ እንዲመዘገብለት ለፍርድ ቤት አቤቱታ ቀርቦ ፍርድ ቤቱም ተቀብሎ ያጸደቀዉ መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ ሲያቀርብ ነዉ፡፡

የተያዘዉ ጉዳይ፣ ከፍ ሲል እንደተመለከተዉ፣ በአዲስ አበባ ከተማ በግዥ የተገኘዉ ኮንዶሚኒየም ቤት የአመልካች እና የተጠሪ የጋራ ንብረት ስለመሆኑ አላከራከረም፡፡ የተጠሪ ክርክር ይህ ቤት የግል ይባልልኝ የሚል ባለመሆኑ ቤቱ የተጠሪ የግል ንብረት ሊሆን ይገባል ወይስ አይገባም የሚል ጭብጥ ሊያዝ የሚችልበት ሁኔታ የለም፡፡ በመሆኑም የክልሉ የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 69 ድንጋጌ ለተያዘዉ ጉዳይ ተፈፃሚነት ያለዉ አይደለም፡፡ ይልቁንም የተጠሪ

ክርክር የግል ንብረቴን ሽጬ ለቤቱ ግዥ በወጣዉ ገንዘብ ላይ ተጨማሪ ያደረግኩ በመሆኑ የግል የሆነዉ ገንዘቤ ይመለስልኝ የሚል ይዘት ያለዉ ነዉ። ስለሆነም በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ አንቀጽ 246(1) መሠረት መያዝ የሚገባዉ ትክክለኛ ጭብጥ የጋራ ነዉ በተባለዉ ንብረት የተጠሪ የግል ገንዘብ የተቀላቀለበት ነዉ ወይስ አይደለም? ህጋዊ ዉጤቱስ ምንድን ነዉ? የሚል ነዉ። ስለሆነም ለጉዳዩ በቀጥታ ተፈፃሚነት ያለዉ ድንጋጌ የክልሉ የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 97(2) ላይ የተመለከተዉ ነዉ። የዚህ ድንጋጌ ሙሉ ይዘትም *"ከባልና ሚስቱ አንደኛዉ የግል ሀብት የሆነ ማናቸዉም ንብረት ለሌላ ሰዉ የተላለፈ መሆኑንና ከዚሁ ግብይት የተገኘዉን ገንዘብ ከጋራ ሀብታቸዉ ጋር የተቀላቀለ መሆኑን ያስረዳ እንደሆነ ከዚሁ ንብረት ጋር ተመጣጣኝ የሆነ ገንዘብ ወይም ንብረት ከጋራ ሀብታቸዉ በቅድሚያ የማንሰት መብት ይኖረዋል"* የሚል ነዉ። ይህ ድንጋጌ ደግሞ አንደኛዉ ተጋቢ የጋራ በሆነዉ ንብረት ዉስጥ የተቀላቀለዉ የግል ንብረቴ ተብሎ ይመዝገብልኝ የሚል አቤቱታ አቅርቦ በፍርድ ቤት ማስጸደቅን የሚጠይቅ አይደለም። ይህ ድንጋጌ ግልጽ በመሆኑ እንዳለ ተፈፃሚ ከማድረግ ዉጪ ትርጉም መስጠት አስፈላጊ አይሆንም። ትርጉም መስጠት አስፈላጊ ሊሆን የሚችልበት ምክንያት ቢኖር እንኳ የንብረት ባለቤትነት ጽንሰ ሃሳብ እና መሠረታዊ መርህን የባልና ሚስት የጋራ ሀብት ተጣርቶ ሊወሰን የሚወሰንበትን ሁኔታ አስመልክቶ በቤተሰብ ህጉ ላይ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች ጋር በተጣጣመ መልኩ ትርጉም መስጠት ያስፈልጋል።

በመሠረቱ የንብረት ባለቤትነት መብት በዓለማችን በተለያየ መልኩ በህግ ዕዉቅና ከተሰጣቸዉ የሰዉ ልጆች መብቶች መካከል አንደኛዉ መሠረታዊ መብት ነዉ። ይህ መብት የተባበሩት መንግስታት ቻርተር እ.ኤ.አ በ1945 ከወጣ በኋላ የመጀመሪያዉ የሆነዉ የሰብአዊ መብቶች ሁሉ አቀፍ መግለጫ እ.ኤ.አ በ1948 ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ በወጡ ዓለም አቀፍ፣ አህጉራዊና ብሔራዊ ሰብአዊ መብት ነክ ሰነዶች ተካቶ ይገኛል። የተባበሩት መንግስታት ያወጣዉ የሰብአዊ መብቶች ሁሉ አቀፍ መግለጫ (Universal Declaration of Human Rights) አንቀጽ 17 ማንም ሰዉ ብቻዉንም ሆነ ከሌሎች ጋር በመተባበር የንብረት ባለቤት የመሆን መብት ያለዉ መሆኑንና ማንም ሰዉ በዘፈቀደ ንብረቱን እንዳያጣ እንደማይደረግ ይደነግጋል። አህጉራዊ የሰብአዊ መብቶች ሰነዶች ከሆኑት መካከል በአፍርካ የሰዎችና የህዝቦች መብቶች ቻርተር ሰነድም የንብረት ባለቤት የመሆን መብት የህግ ዋስትና ያለዉ መሆኑን ይደነግጋል። ኢትዮጵያ ዋነኞቹን በሰብአዊ መብቶች ላይ ያተኮሩ አለም አቀፍ ሰነዶችን ያጸደቀች ከመሆኗም በላይ በህገ መንግስቷ ዉስጥ ዕዉቅና በመስጠት የአገሪቷ የህግ አካል አድርጋቸዋለች። በኢፌዲሪ ህገ መንግስት ማንኛዉም የኢትዮጵያ ዜጋ የግል ንብረት ባለቤት መሆኑ/መሆኗ እንደሚከበርለት/እንደሚከበርለት (Every Ethiopian citizen has the right to the ownership of private property) ሲደነግግ የንብረት ባለቤትነት ምንጭ ደግሞ አንድ ሰዉ በጉልበቱ፣ በመፍጠር ችሎታዉ ወይም በካፒታላቸዉ ያፈሩት (is produced by the labor, creativity, enterprise or capital of an individual) ሀብት ስለመሆኑ በኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 40(1 እና 2) ላይ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል። ይህ ድንጋጌ ዲሞክራሲያዊ መብት ተብለዉ ከሚታወቁት መብቶች ዉስጥ የሚገኝ በመሆኑ በማንኛዉም ደረጃ የሚገኙ የፌዴራል መንግስትና የክልል ህግ አዉጪ፣ ህግ አስፈፃሚ እና የዳኝነት አካሎች የማክበርና የማስከበር ኃላፊነትና ግዴታ ያለባቸዉ መሆኑን በአንቀጽ 13(1) በአስገዳጅነት ተደንግጓል።

የፌዴራልም ሆነ የክልል ቤተሰብ ህግ ባልና ሚስት ጋብቻቸዉን በሚፈጽሙበት ጊዜ በየግል የነበሯቸዉ ንብረቶች ወይም ከጋብቻ በኋላ በዉርስ ወይም በስጦታ በየግላቸዉ ያገኙዋቸዉ ንብረቶች የግል ንብረቶቻቸዉ ሆኖ እንደሚቀሩ፣ የግል ይባልልኝ የሚል አቤቱታ ቀርቦ በፍርድ ቤት የጸደቀ እንደሆነ ባልና ሚስት ከተጋቡ በኋላ አንዱ የግል

ሀብቱ በሆነ ንብረት ለዉጥ ያገኘዉ ወይም በግል ገንዘብ የገዛቸዉ ወይም የግል ንብረቱን ሸጦ የሚያገኘዉ ገንዘብ የግል ሀብቱ እንደሚሆን በፌዴራል የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 57 እና 58 እንዲሁም በአማራ ክልል ቤተሰብ ህግ አንቀጽ 68 እና 69 ላይ ተመልክተዋል። የባልና ሚስት የጋራ ሀብት ለሁለቱም ተጋቢዎች እኩል የሚከፋፈል መሆኑን በክልሉ ቤተሰብ ህግ አንቀጽ 101 ላይ እንዲሁም በፌዴራል የቤተሰብ ህጉ አንቀጽ 90 ላይ ተመልክቷል። ከዚህ የምንረዳዉ ከባልና ሚስት አንደኛዉ ተጋቢ በሌላኛዉ ተጋቢ ንብረት ሰዉ ያላግባብ እንዲበለጽግ ወይም ከጋብቻ በፊት አንደኛዉ ወገን በግል ጥረቱ ባፈራዉ ንብረት ላይ ያለዉ የባለቤትነት መብት ያላግባብ እንዲገደብ የቤተሰብ ህጉ የማይፈቅድ መሆኑን ነዉ።

የባልና ሚስት ተጣርቶ የሚወሰንበትን ሁኔታ አስመልክቶ በፌዴራልም ሆነ በክልል የቤተሰብ ህጎች የተመለከቱት ደንቦች ማለትም ባልና ሚስት በጋራ ሲኖሩ የተፈራ ንብረት መኖሩ ከተረጋገጠ ይህ ንብረት የባልና ሚስት የጋራ ንብረት ተብሎ እንደሚገመት፣ በአንደኛዉ ተጋቢ የግል ንብረት በግብይት ተላልፎ ወይም ተሸጦ የተገኘ ንብረት የግል ሆኖ እንዲቀር በፍርድ ቤት የጸደቀ እንደሆነ የተጋቢዉ የግል ሆኖ እንደሚቀጥል በፌዴራልም ሆነ በክልል የቤተሰብ ህጎች የተመለከቱ ድንጋጌዎችም ቢሆኑ፣ ባልና ሚስት በጋራ ሲኖሩ የተፈራ ንብረት በማን እንደተፈራ ማረጋገጥ ቀላል ባለመሆኑ በማስረጃ አቀራረብ ረገድ ሊኖር የሚችለዉን ክፍተት ለማስቀረት በሚል ዓላማ እንጂ አንደኛዉ ተጋቢ ከጋብቻ ዉጪ በግል ጥረቱ ያፈራዉ ንብረት ሌላዉ ወገን እንዲጋራዉ እና ያላግባብ እንዲበለጽግ የማድረግ ዓላማ የለዉም። ስለሆነም ከባልና ሚስት ንብረት ጋር በተያያዘ ክርክር ሲኖር ፍርድ ቤቶች የሚሰጡት ትርጉም ይህንኑ መርህ ከግምት ዉስጥ ያስገባ ሊሆን ይገባል የሚል ሃሳብ አለኝ።

ሲጠቃለል የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠዉ እና ለዚህ ሰበር አቤቱታ ምክንያት የሆነዉ ዉሳኔ ሲታይ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር አንቀጽ 10(1/ሐ) ላይ የተመለከቱትን ዓይነት ጥሰቶች የተፈጸሙበት መሆኑን የሚያሳይ ይዘት የሌለዉ በመሆኑ በዚህ ሰበር ሊታረም የሚችል መሠረታዊ የህግ ስህተት ባለመኖሩ በዚህ ደረጃ ሊታረም የሚገባዉ አይደለም። ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተዉ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተጠሪን መሠረታዊ ክርክር ባገናዘበ መልኩ ጉዳዩን ከክልሉ የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 97(2) አንፃር መርምሮ ዉሳኔ መስጠት ሲገባዉ ተጠሪ ገንዘቡ የግሉ መሆኑን ማስመዝገብ ነበረበት የሚል ምክንያት በመስጠት የሰጠዉን ዉሳኔ በማረም፣ ለጉዳዩ ተፈፃሚነት ያለዉ የቤተሰብ ህጉ አንቀጽ 97(2) እንጂ አንቀጽ 69 አለመሆኑን በመጥቀስ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ ተገቢ ነዉ ከሚባል በስተቀር በዚህ ችሎት ሊታረም የሚችል መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ባለመሆኑ ሊጸና ይገባል የሚል ሃሳብ ስላለኝ ከአብላጫዉ ድምጽ በሃሳብ ተለይቻለሁ።

የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት

መ/0